

# ጴጥሮስ ከእስር ቤት አመለጠ

- ንጉስ ሄሮድስ ክፉ ንጉስ ነበር። ክርስቲያኖችን ከማሳደድ አልፎ የጴጥሮስ ወንድም የሆነውን ሐዋርያው ያዕቆብን አስገድሎታል። አይሁዳውያን በዚህ መደሰታቸውን ስላየም ጴጥሮስን አሳሰረው።

- ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንደማያመልጥ እርግጠኛ ለመሆን ከእርሱ ጋር በእስር ቤት ውስጥ ጠባቂዎችን አብሮ አስቀመጠ። በ24 ሰዓት ውስጥ በአራት ፈረቃ ጴጥሮስን የሚጠብቁ አራት አራት ጠባቂዎች ተመድብለውት ነበር። በምንም አይነት መንገድ ጴጥሮስ ከእስር ቤት ማምለጥ የሚችልበት ምንም አይነት አመቺ ሁኔታ አልነበረም። በእርግጠኝነት በሚቀጥለው ቀን ለፍርድ ይቀርባል።

- በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስርቲያን አጥብቃ ጴጥሮስ እንዲፈታ ወደእግዚአብሔር ትፀልይ ነበር። ክርስቲያኖች ተመልሶ እንዲመጣ ይፈልጉ ነበር። ጴጥሮስ በእስር ቤት ውስጥ እንቅልፍ ይዞት ነበር። ሁለቱም እጆቹ በሰንሰለት ታስረው ነበር። በግራውም ሆነ በቀኙ ጠባቂዎች ነበሩ። ከዚያም በላይ በመውጫው ላይ ተጨማሪ ወታደሮች ነበሩ።

- ለእግዚአብሔር የሚከብደው አንዳችም ነገር የለም። በድንገት አስደናቂ ብርሃን ወህኒውን ሞላው። አንድ የእግዚአብሔር መልአክም ታየ። መልአኩም የጴጥሮስን ጎን መታ አድርጎ ቀሰቀሰው። የጴጥሮስ ሰንሰለትም ተበጣጠሰ።
- “ተነስ፤ፍጠን!” አለው ጴጥሮስን መልአኩ። ጴጥሮስ መልአኩ እንዳዘዘው ልብሱን ለበሰ፤ መጫሚያውንም አጠለቀ። ከዚያም እርሱን እንዲከተለው አዘዘው። ጴጥሮስም መልአኩን ተከተለው። ሆኖም እውነት አልመሰለውም። ሕልም መሰለው እንጂ!

- የመጀመሪያውን ጠባቂ አለፉ። ሁለተኛውንም ጠባቂ አልፈው ሄዱ። ጠባቂዎቹ ግን አላዩአቸውም። ተኝተው ይሆን ወይንስ የሚሆነውን ነገር ለማየት አይናቸው ታውሮ ነበር?

- አሁን ጴጥሮስ ከእስር ነፃ ለመውጣት አንድ እንቅፋት ብቻ ይጠብቀዋል። ወደ ከተማይቱ የሚያመራው የብረት መዝጊያ ፊት ለፊታቸው ነው። መዝጊያውም ማንም ሳይነካው በራሱ ወለል ብሎ ተከፈተ። በተከፈተው መዝጊያ አልፈውም በጎዳናው ጉዞአቸውን አቀኑ። በድንገት እንደተገለጠ አሁንም መልአኩ በድንገት ጴጥሮስን ትቶት ሄደ።

- ጴጥሮስም ፀጥ ረጭ ባለው ጎዳና ብቻውን መሆኑን ተረዳ። ህልም እንዳልሆነና እግዚአብሔር ከንጉስ ሄሮድስ እጅ ከፉ ምክር እንዳዳነው ተረዳ።

- ስለዚህም ወዳጆቹን ፍለጋ በፍጥነት ከዚያ ስፍራ ሄደ። በቀጥታ ያመራውም ክርስቲያኖች ተሰብሰበው ስለእርሱ ወደሚፀልዩበት ወደማርቆስ እናት ወደማርያም ቤት ነበር። በቤቱ ደጅ ቆሞ አንኳኳ። ሮዳ የምትባል ገረድ በሩን ለመክፈት ሄደች። “ማነው?” ብላ ብትጠይቅ የሚያስደንቅ ነገር አደመጠች! ጴጥሮስ “እኔ ነኝ፣” አላት። እርሷም የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑ ገባት። በጣም ከመደነቋ የተነሳ በሩን አልከፈተችም። ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች ሄዳ “ጴጥሮስ በደጅ ቆሞ እያንኳኳ ነው!” አለቻቸው።

- እነርሱም ያበደች መሰላቸው። እንዴት ጴጥሮስ ሊሆን ይችላል? ጴጥሮስ በወህኒ ውስጥ ነው የነበረው። “የጴጥሮስ መልአክ ሊሆን ይችላል፣” አሉ። አይሁዳውያን በዚያን ዘመን እያንዳንዱ ሰው የራሱ መልአክ እንዳለው ያምኑ ስለነበር የጴጥሮስ መልአክ በጴጥሮስ ድምፅ እየተናገረ ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ።

- ጴጥሮስ ግን ማንኳኳቱን አላቋረጠም። በመጨረሻም በሩን ቢከፍቱት ጴጥሮስን ቆሞ አዩት። ጴጥሮስ እንዲፈታ በእግዚአብሔር ፊት ያቀረቡትን ልመና እግዚአብሔር እንደሰማ አላመኑም ነበር ማለት ነው?

- በዚያ ተሰብስቦ የነበረ ሰው ሁሉ በአንድነት ማውራት ጀመረ። ጴጥሮስም ሁሉ ፀጥ እንዲሉ በእጁ ምልክትን ሰጣቸው። ከዚያም እንዴት እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከእስር ቤት እንዳስመለጠው ነገራቸው።

- ለያዕቆብና ለሌሎችም ይህን እንዲነግሯቸው አሳሰባቸው። ምናልባትም ይኸኛው ያዕቆብ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ሌላኛው ያዕቆብ በሄሮድስ ተገድሏልና።

- በሚቀጥለው ቀን ማለዳ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ምን የሆነ ይመስላችኋል? ጴጥሮስን በወህኒ ቤቱ ውስጥ በሁሉም ቦታ ፈለጉት። የወህኒው ጠባቂዎች ጴጥሮስን የመጠበቅ ኃላፊነት ነበረባቸው። ሆኖም ኃላፊነታቸውን በማይወጡ የወህኒ ጠባቂዎች ላይ ፍርዱ ሞት ነበር። ስለዚህ ሄሮድስ አራቱ የወህኒ ቤት ጠባቂዎች በሞት እንዲቀጡ ወሰነ።

- ከጥቂት ቀናት በኋላም ሄሮድስ ንግግር ለማድረግ ሕዝብ በሰበሰበበት ቦታ ተገኘ። ሕዝቡም፣ “ ይህ የእግዚአብሔር እንጂ የሰው ድምፅ አይደለም!” አሉ። ሄሮድስም ለእግዚአብሔር የሆነውን ምስጋና ስለተቀበለ የእግዚአብሔር መልአክ ወዲያው ተገልጦ መታውና በትል ተበልቶ ሞተ።

*ይህ የጴጥሮስን ከእስር ቤት የማምለጥ ታሪክ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 12፡ 1 – 18 ውስጥ ማንበብ ይቻላል።*

Copyright picture courtesy of gospelservices.com

http://gardenofpraise.com